# Press Release

Embassy of the United States of America
Addis Ababa, Ethiopia
*2016/33*

For further information, call 011-130-7033
http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ( USAID) ብሔራዊ የኤድስ መረጃና የምክር አገልግሎት ማዕከል ለኢትዮጵያ መንግሥት አስረከበ

***አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፤ሰኔ 23 ቀን 2008 ዓ.ም*፡-**የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (USAID) ከጆን ሆፕኪንስ የተግባቦት መርሀ ግብሮች ማዕከል ጋር በመሆን የኤጀንሲውን የጤና ተግባቦት አቅም ግንባታ የጋራ ፕሮጀክትን ቁልፍ እንቅስቃሴዎች በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል ለኢትዮጵያ መንግሥት አስረከበ፡፡ ይህ በጆን ሆፕኪንስ ዩኒቨርስቲ የሚመራው ፕሮጀክት ብሔራዊው ወገን የጥሪ ማዕከል አገልግሎትን፣ በኤድስ ዙሪያ የተለያዩ ግብዓቶችን የሚያቀርብ ቤተ መጻሕፍትን፣ በበርካታ አድማጮች ያሏቸው ኤች አይ ቪን በመከላከል ላይ የሚያተኩሩ የሬዲዮ ፕሮግራሞችን፤ እንዲሁም በጤና ጥበቃ በኩል በማኅበራዊ ባሕርይ ለውጥ ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ጨምሮ ዘርፈ-ብዙ እንቅስቃሴዎች የተካተቱበት ነው፡፡

በኤድስ ዙሪያ የተለያዩ ግብዓቶችን የሚያቀርበው ማዕከል፤ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች፣ ለማኅበረሰብ-አቀፍ ድርጅቶች፣ ለተመራማሪዎች፣ ለሃይማኖት መሪዎች፣ ለመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ለጋዜጠኞች፣ በኤች አይ ቪ ለተጠቁ ግለሰቦች፤ እንዲሁም ለተማሪዎችና ሌሎች የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፤ በኤች አይ ቪ ዙሪያ ትክክለኛና ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡ ይኸው ማዕከል በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ይገኛል፡፡

የጥሪ ማዕከሉ በወር እስከ 300,000 ጥሪዎችን ሲያስተናግድ የቆየ ሲሆን፤ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ለተጠቁ ደዋዮችም ነፃ የማማከርና የሥነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ 90 በመቶ የሚሆኑቱ ደዋዮች ከ15-29 የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ነበሩ፡፡ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ በተጨማሪ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሌሎች ጤና ነክ ጉዳዮች ዙሪያም የምክር አገልግሎቶችን ለመስጠት ዕቅድ ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

የፕሮጀክቱ አካል የሆነው ቤተኛ የተሰኘው የሬዲዮ ፕሮግራም፤ በኤች አይ ቪ/ኤድስ የተጠቁ ሰዎች የሚያጋጥማቸው መድሎና መገለል ላይ በማተኮር በርካታ ርዕሰ-ጉዳዮችን ይዳስስ ነበር፡፡ በየሳምንቱ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ግለሰቦችን ድምፅ በአምስት የሬዲዮ ጣቢያዎች አማካይነት፤ በሦስት ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ፣ በኦሮምኛና በትግርኛ ወደ አድማጩ ኅብረተሰብ ሲያደርስ ቆይቷል፡፡ ሌላው ዳጉ የተሰኘ ፕሮግራም በአዲስ አበባ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ በሚገኙ ወጣቶች ላይ በማተኮር በኤች አይ ቪ/ኤድስና ለሕይወት ስንቅ በሆኑ ክህሎቶች ዙሪያ ቁልፍ መልክቶችን በማስተላለፍ ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር ርክክቡ በተካሄደበት ወቅት ባደረጉት ንግግር፡- “የኢትዮጵያ መንግሥት ይህ የርክክብ ሂደት ይሳካ ዘንድ በባለቤትነት መምራቱ ለሌሎች ፕሮግራሞችም እንደ ጥሩ ተሞክሮ የሚወሰድ ነው” ብለዋል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ላለፉት 12 በላይ ዓመታት ከአሜሪካ መንግሥት የፕሬዚዳንቱ አስቸኳይ የኤድስ እርዳታ መርሀ ግብር (PEPFAR) በተደረገለት የገንዘብ ድጋፍ ኢትዮጵያ ኤድስን ለመዋጋት ስታደርግ የቆየችውን ጥረት ደግፏል፡፡ ኤጀንሲው አሁንም እነዚህንና መሰል የጤና አገልግሎቶችን በተመሳሳይ መልኩ በጆን ሆፕኪንስ በሚተገበረው በዚህ የጤና ተግባቦት እንቅስቃሴ በኩል መደገፉን ይቀጥላል፡፡

የጤና ተግባቦት አቅም ግንባታ የጋራ ፕሮጀክቱን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ቢያስፈልግዎ ቀጥሎ በተመለከተው የኢ-ሜይል አድራሻ ለአምሪታ ጊል-ባይለይ ይጻፉ፡-agbailey@jhu.edu፡፡

***